

ደጃች ካሳ የሮኬቶች ተኩስ ልምምድ ሲመለከቱ
(ዋቢ. መፅሐት ተ.ቁ. 16)

# የምዕራፍ አምስት ማስታወሻዎች

**ቁጥር 73፤** ይህ አዋጅ እንደተነገረ፣ ካሳ ምርጫና ዋግሹም ጎበዜ ለኮሎኔል መርዌዘር ደብዳቤ ልከዋል። ለእንግሊዞቹ፣ ይህ አዋጅ ከታሰበው በላይ በጣም ጥሩ ውጤት ነበር ያስገኘላቸው። ምናልባትም፣ ደጃዝማች ካሳም ሆነ ዋግሹም ጎበዜ የእንግሊዞቹን አመጣጥ በቅኝ ገዥነት ቢያዩት ይዋጉ ነበር ወይ? በርግጥ፣ ደጃዝማች ካሳ ጥቃት ያደርሳሉ ተብሎ ተፈርቶ ነበር። ደራሲውም ቢሆን ይህንን ይገልጣል። የምፅዋ ገዥ የነበረው ግብፃዊ ሁሴን ቤይ የምፅዋውን ናይብ መሀመድን ደብዳቤ አሲዞ ወደ አድዋ ልኮት ነበር። ይህ የሆነውም የእንግሊዙ ሜጀር ግራንት ከደጃች ካሳ ጋራ በተገናኙበት ወቅት ነበር። የምፅዋው ገዥ የሀገሩን ተወላጆች(አቢሲኒያኖቹን) እንግሊዞቹን እንዳይረዱ እንዲያውም እንዲዘርፉ፣ ደጃች ካሳን ቢሆን ዘመቻውን እንዲቃወሙ መከሯል ተብሎ፣ የግብፁ አድሚራል ምፅዋ ለጉብኝት ሲመጣ፣ ሰውየውን ከሥልጣን አስነስቶታል። እንግሊዛዊው ፀሀፊ፣ ሔንሪ ሆዚየር፣ ከሥልጣን መነሳቱ ይገባዋል ይላል።

**ቁጥር 74፤** ቴዎድሮስ፣ በታህሳስ 2 እንግሊዞች ዙላ ማረፋቸውን ሰምተዋል። በ20 ደግሞ በአማርኛ የተፃፈው ይህ የናፒየር አዋጅ በትግራይ በኩል ደርሷቸዋል። የተፈራው፣ ቴዎድሮስ ተናደው የአውሮፓ ባለሟሎቻቸውን በሙሉ ያስራሉ ተብሎ ነበር። ነገር ግን፣ ቴዎድሮስ ፈገግ ብለው ደብዳቤውን ለማንም፣ ለፀሐፊያቸው ለአለቃ እንግዳ እንኳን ሳያሳዩ አስቀምጠውታል። እኔ በሥጢኋቸው የቆርቆሮ ሣጥን ውስጥ ነው ያስቀመጡት ይላል ራሳም። የሚገርመው ይህን የናፒየር አዋጅ ለራሳም የላኩለት ዋግሹም ጎበዜ ነበሩ።

**ቁጥር 75፤** ደጃች ካሳ (በኋላ አፄ ዮሐንስ) ሙሉ ስማቸው ካሳ ምርጫ (በዝብዝ ካሳ) ሲሆን፣ እንግሊዞቹ የልዑልነት (መስፍን) ደረጃ አላቸው በሚል ልዑል የሚለውን ማዕረግ ስለሠጡ፣ ፀሐፊው፣ ልዑል ካሳይ አያሰም ይጠራቸዋል።

**ቁጥር 76፤** ይህ ደብዳቤ የንጉሣዊ ማህተም እንዳለበት ተገልጧል። መርዌዘር፣ ማህተሙን ያላየ በመምሰል ሳይጠቅስ መልስ እንደላከ ተዘግቧል። (Record of the Expedition to Abyssinia) ይህ፣ ገና ሳይነግሱ፣ ራሳቸውን ንጉሥ እያሉ በመጥራት ማህተም ማሰራት በደጃች ካሳ ብቻ ሳይሆን በሌሎቹም፣ ምኒልክን ጨምሮ የሚታይ ነገር ነበር። ለዚህ ደብዳቤ ምላሽ የተሠጠው ከኮሎኔል መርዌዘር ነበር። የደብዳቤው ሙሉ ቃል እንደሚከተለው ነበር። በታህሣስ 5 ነበር የተፃፈው።

**እ**ንደምናሉ፤ ደህና ነዎት ወይ?
**የ**ፃፉት ደብዳቤ ደርሶናል፤ ከፍተኛ ደስታ ነው የሠጠን። ከዚህ ቀደም ሁለት **ደ**ብዳቤዎች ልከንልዎት ነበር፤ ነገር ግን ከርስዎ ባለመድረሳቸው በጣም እናዝናለን።

እነዚያን ሁለት ደብዳቤዎች ስንልክ፣ በመሀከላችን፣ ከራስ ሚካኤል፣ ወልደስላሴ እና ሰባጋዲስ ጀምሮ በነበረው ወዳጅነት ዕውቀት በመተማመን ነው፡፡ አሁን ወደ ሰናፌ እየተጓዝን ነው፤ ጄኔራል ሮበርት ናፒየር እስከሚመጣ በዚሁ ቦታ እንቆያለን፡፡ እስከዚያ ድረስ ግን በመሀከላችን ያለውን ትልቅ ወዳጅነት መሠረት በማድረግ ከዚህ ቀጥሎ የምንልከልዎትን እዋጅ በርስዎ ግዛት እንዲያለነግሩ እንለምንዎታለን፡፡

ሌላው በጣም ትልቅ ነገር፣ የሚያስፈልጉን ነገሮች፣ ለንዴ፣ ገብስ፣ እህልና ሌሎችንም አስፈላጊ ነገሮች፣ እንዲሁም ብዛት ያላቸው በቅሎዎች ጨምሮ ነው፡፡ ለነዚህ ሁሉ ተመጣጣኝ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኞች ነን፡፡

የምንጠይቅዎት ነገር፣ በመልካምነት እስዎ ይህንን ጉዳይ ለአለቆችና ለገበሬዎች እንዲታውቅ እንዲያደርጉና ሰዎችም የተባሉትን ነገሮች ለኛ እንዲያቀርቡ ነው፡፡

ልጅ ምርጫ ከኛ ጋር ቢሆን ደስታችን ነው፡፡ በመሀከላችን ላለው ግንኙነት ጠቃሚ ስለሚሆን ፈቃድ እንዲሠጡት እንጠይቃለን፡፡

***ቁጥር 77፣*** *ምርጫ ወርቄ በህንድ አገር በቦምቤይ የተማረ ሰው ነበር፡፡ ሄንሪ ዱፍተን፣ ምርጫን ከከረንስ ጋር ምፅዋ በእንግሊዝ ቆንስላ ጽ/ቤት እንዳገኛቸው ገልጦ፣ ቆንስላው ካሜሮን፣ ወደ ሱዳን ለስራ በሄደበት ጊዜ ሁለቱም ተወካይ ሆነው ይሰሩ ነበር ብሏል፡፡ የደጃዝማች ካሳ መልክተኛ ሆኖ ወደ እንግሊዞች ካምፕ የሄደው ይህ ራሱ ምርጫ ነው፡፡ የሰውየው በምቤይ መማርም በእንግሊዞቹ የዘመቻ ዘገባቸው ተገልጧል፡፡ ራሳምም፣ ይህንን በማረጋገጥ፣ ምርጫ ወርቄ ቦምቤይ እንደተማረና በምፅዋም በእንግሊዝ ቆንስላ ተቀጥሮ ይሠራ እንደነበር ይገልፃል፡፡ ራሳም፣ ምፅዋ ሲደርስ ምርጫ ወርቄን አብሮት እንዲሠራ ልኮበት ነበር፤ ሆኖም ምርጫ ቴዎድሮስን ፍራቻ ፈቃደኛ አልነበረም፡፡*

***ቁጥር 79፣*** *ፋቢየስ ክንክታቶር በ280 ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረ የታወቀ የሮማ ፖለቲከኛና የጦር ጄኔራል ነበር፡፡ ጄኔራሉ የሽምቅ (ጎሬላ) ውጊያ መስራች እንደሆነ ነው የሚነገረው፡፡ እንግሊዞቹ፣ ደጃች ካሳን የፈሩበት ምክንያት፣ ገና ጦራቸው ሰናፌ እያለ በተለያዩ መልክተኞች በኩል፣ ካሳ 8ሺ ጦር ይዞ የእንግሊዞች ጦር ወደሀገሩ እንዳይገባ ይከላከላል የሚል ዜና ደርሷቸው ስለነበረ ነው፡፡ (Record of The Expedition to Abyssinia)፡፡ የእንግሊዞ መልክተኛ ሜጀር ግራንትም ደጃዝማች ካሳ ላይ ጥሩ አመለካከት አልነበረውም፡፡ ካሳ ምርጫ በዚያን ጊዜ የሀያ ስድስት አመት ዕድሜ ያላቸው ወጣት ነበሩና ቁርጠኛ ሀሳብ አያሳዩም በማለት ነበር፡፡ እንደ መርካም ገለፃ፣ ከእንግሊዞቹ ጋር ወዳጅነት መፍጠሩ ጠቃሚታ እለው ብለው የወሰኑት የካሳ አማካሪዎች ናቸው፡፡ አንድ ግልፅ የተደረገ ነገር ቢኖር፣ እስፈሪውን ቴዎድሮስ እንግሊዞቹ ራሳቸው ወይም ብቻቸውን እንደሚወጉ ነው፡፡ በካሳ በኩል ግን ቀለብና ከብት በግዥ እንደሚቀርብ፡፡ ከዚያም እንግሊዞቹ ሲመለሱ መሳሪያዎች እንዲሠጡት ነበር፡፡*

# ምዕራፍ ስድስት

አንጣሎ - የገበያ አይነት

በአንጣሎ[85]፣ አኔና ሰመልፌንገስ፣ በሰንቅና ትጥቅ ከፍሉ ሀላፊው በሌተናል ኮሎኔል ፋይሪ የሚመራውን ቀዳሚ ጦር አገኘን፡፡ ከአሁን በኋላ እንደፈለግነው በሀገሩ ውስጥ መንቀሳቀስ አንችልም፤ የወደፊት ጉዟችን ከጦሩ ጋር ነው የሚሆነው፡፡

ከዙላ እስከ አንጣሎ የጋጠመኝንና ያየሁትን በዝርዝር ገልጫለሁ፡፡ ይህም ከወታደሮቹ ተለይተን ለብቻችን ስለምንጓዝ ነበር፡፡ ከትክክለኛው የዘመቻ እውነታ ጋር ገና አልተዋወቅንም፡፡

ጦሩ አንጣሎ እስከሚመጣ ድረስ፣ በሀገሩ ውስጥ እንደልቤ እየጋሰብኩ፣ ጅብና ተኩላ እያሳደድኩ ራሴን እስደስቼ ነበር፤ በአካባቢው ያሉ መንደሮችን እየጎበኘሁ ቅቤ፣ ዳቦ፣ ወተት፣ ዶሮ እየገዛሁ፣ ወይም አሜሪካ ሳደርግ እንደነበረው ሁሉ ምግብ ያለበት ቦታ እየዞርኩ ነበር፡፡

በአንጣሎ፣ ዕሮብ ገበያ ስለሚውል የአካባቢው ገበሬዎች የሚሰባሰቡበት ቀን ነው፡፡

አሁን ባለንበት ካምፕ በደረስን በመጀመሪያው ዕሮብ ቀን፣ ከካፒቴኑ ጋር በመሆን ይህንን መገናኛ ቦታ ለማየት ወጣን፡፡ በዚህ ቀን የአቢሲኒያ ምርጥ ሰዎች ይገኙበታል ይባላል፡፡

ለካምፕ እንዲሆን የተቀየሰው ሰፍራ በሜዳማው ቦታ መሀሉ ላይ ነው፤ ይህም በምዕራብ በኩል ከአንጣሎ እስከ አፍጎል የተዘረጋ ነው፤ በምስራቅ በኩል ወደ አሰራ እምሰት ማይሎች ርቀት ላይ ሲሆን፣ በአንጣሎና በጥንታዊና አስገራሚ በሆነው በጨለቆት ከተማ እኩል ርቀት መሀል ላይ ነው፡፡ የጉንዳዋ ወንዝ በበጋ ጊዜ ቢደርቅም በካምፑ ምዕራባዊ ዳርቻ ይወርዳል፡፡ ይህ የሚመች አገር፣ ሳሩ ረዥም በመሆኑ፣ በዘመቻው የመጡት ከብቶች በሙሉ በቂ ግጦሽ አግኝተዋል፡፡

ጉንዳዋን እንደተሻገርን፣ ፈረሶቻችን ኮልኩለን በፍጥነት መጋለብ ጀመርንና አንድ ሰአት በፈጀ ጊዜ ከተያያዙ ተራሮች ሥር ደረስን፡፡ ተራሮቹ፣

---

[85] አንጣሎ፣ ተጨማሪ ማስታወሻዎች ምዕራፍ



የአንጣሎ ገበያ
(ዋቢ. መፅሐፍ ተ:ቁ. 16)



በእንጣሎ የሚገኝ መንደር
(ዋቢ መፅሐፍ ተ.ቁ. 16)

ከተማውን ትተን ቤተክርስቲያኖቹን ለመጎብኘት ሄድን፡፡ ከውጭ ሊመለከቷቸው በአረንጓዴ ዛፎች ተከበው በጣም ውበት ነበራቸው፡፡ እየተጠጋን ስንሄድ ግን፣ በሩቅ ያየነው ውበት እየደበዘዘ ይሄዳል፡፡ ከውጭ በኩል በረት ነበር የሚመስለው፤ ውስጥ ስንገባም የተሻለ አልነበረም፡፡ ከአጠገቡ በሚገኝ ቤት ውስጥ ቄሱ ይኖርበታል፡፡ አውሮፓውያኖች መምጣታችን ሲያይ፣ የቤተክርስቲያኑን ውስጥ ካሳየን በኋላ ወደቤቱ እንድንገባ ለመነን፡፡ ገብተን ከተቀመጥን በኋላ፣ በዋንጫ አርጎና የፍየል ወተት አቀረበልን፡፡ ከዙላ እስከ አንጣሎ ድረስ ያላየነው ነገር ስለነበረ በአንግዳ ተቀባይነቱ በጣም ተገረምን፡፡ ያም ሆነ ይህ፣ የተሠጠንን የሚጥም መጠጥ ጠጣን፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ፅሁፎችና መፃሕፍት አመጣልንና ሊሸጥልን እንደሚፈልግ ነገረን፡፡ ከነበረን ጉጉትና ከሰብሰናቸው ዕቃዎች ለመጨመር ብዙም ስሜት ባይስጠንም ግማሽ ደርዘን የሚሆኑትን ከጓደኛዬ ጋራ ገዛን፡፡ ለመሄድ ስንነሳ፣ ቄሱ፣ ለወተቱ መክፈል አለመፈለጋችን ጠየቀን፡፡ ለመክፈል እንኳን አላሰብንም፤ ነገር ግን፣ በመልካም ሁኔታ፣ ብንከፍል የሚቀበለው ነገር መሆኑን ጠቆም ስላደረገን፣ ለመፃሕፍቱ ሁለት ዶላር ብንከፍልም፣ ምንም ሳንቅማማ ለወተቱም ከፈለን፡፡

ወደ ካምፕ ከመመለሳችን በፊት፣ እኔና ካፒቴኑ ጓደኛዬ ለአደን ወደ ተራራዎቹ አመራን፡፡ ጥንቸሎች በብዛት አሉ፤ ቆቅና ዥግራዎች በየቦታው ነበር የሚበሩት፤ ሚዳቋዎችም ቢሆን በአካባቢያች ሲፈናጠሩ ነበር፡፡ ጓደኛዬ ክርክሮ አይቻለሁ ብሎ ሊያሳምነኝ ሞክሮ ነበር፡፡

ወደ ካምፕ ፊታችን ከማዞራችን በፊት ቀኑ እየመሸ ነበር፡፡ ብዙ ቦታዎችን አካልለናል እና የሚያስደስቱ የተራራ ዕይታዎችና ገላጣ መሬቶችን አይተናል፡፡ ቀኑ እየተገባደደ፣ ምሽቱ በችኮላ እየመጣ፣ ፀሀይዋም በግርማ፣ ራቅ ባለና በሰፋው መሬት ላይ እየጠለቀች፣ በሜዳማው መሬት ላይ ብጫማ ደብዘዝ ያለ ብርሀን እያበራች፣ ራቅ ያሉ ተራሮች ላይ ደግሞ ወይን ጠጅ የመሰለ ቀለም ስትቀባ፣ በተራሮቹ ስር ያሉ ገደሎችና መንገዱ ላይ ደግሞ ጥላ እያጠላ ነበር፡፡

ውድ ጓደኛዬ ካፒቴኑ፣ ከዚህ ቀደም ስላደረጋቸው አስደናቂ ገጠመኞቹ በማጫወት ትኩረቴን ሊስበው ሞክሯል፡፡ እንደ አወራሩ ከሆነ አውነቱን የሚናገረ ሰው ለመሆኑ መረጃ ነበር፡፡ በርግጥ፣ ለመናገር ያለው ስሜት በማንኛው ጌዜና ቦታ ይገለጥ ነበር፡፡ እንዲህ ያለ አዋቂ ሰው መኖሩን ማወቅ ደግሞ በመጠኑም ቢሆን የኔ ድርሻ ነበር፡፡ ለለ ጓደኛዬ፣ በአእምሮዬ ሃሳብ ውል ሊልብኝ፣ ትልቅ ሥልጣን ያለውና ሰፊ ሀብት ያለው መሆኑን ሳስታውስ ደስ የሚል ሀሳብ ሊኖረኝ የሚገባውን ሁኔታ ያዘናጋኛል፤ ነገር ግን፣ ይህ፣ መጠነኛ አንግዳ የሆነ የአእምሮ ለውጥ ብቻ ነበር፡፡

"አሃ፣ ይቅርታ አደርግልኝ፣ የተነሳሳህ መሰሎኝ ነበር፤ ሆኖም የዕይታ መደናገር ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን ምን አይነት አውሬ ነው ለመሆኑ የተኮሰከበት?"

"ጠመንጃየን ጥይት እስከማጎርስ ድረስ፣ እባክህ ራስህ ምን እንደሆን እየው::"

"እንዴት፣ ጅብ ነው::" አልኩ:: የወደቀውን አውሬ ለተወሰነ ጊዜ ካስተዋልኩ በኋላ፣ በሆዴ ግን፣ እሱ ራሱ ቢያየው ተመኝቼ ነበር::

"ጅብ? ነው እንዴ? አሆ ሆ! ብዙ ጊዜ ጅቦች ከግሥላ በላይ አደገኛ ናቸው:: ለምሳሌ፣ በጥርሳቸው አንዴ ከያዙ ምንም ቢሆን አይለቁም::" ይሄን እየተናገረ በመራመድ ወደ ወደቀው አውሬ ተቃረበ:: ጭንቅላቱ አጠገብ ሲደርስ አውሬው ቀና ማለት ጀመረ፤ ካፒቴኑ ጠመንጃ ቢይዝም፣ በማያወላውል ሁኔታ ትንሽ ተደናግጦ ነበር:: በጅቡ በኩል የጣዕረ ሞት ነበር፤ በካፒቴኑ በኩል ደግሞ የአዳኞች ጣዕር ነበር:: አውሬው የመጨረሻ እስትንፋሱን ሲያቆም፣ "ቀልደኛው ሽማግሌ"፣ የአውሬውን አስከሬን፣ ጭንቅላቱን መርጦ ተኮሰበት:: "ለማረጋገጥ፣ ለመጨረስ ነው፣ ታውቃለህ::" አለ::

ወደ ካምፕ ስንመለስ መሽቶ ነበር፤ ጓደኛዬ ጅብ ከመግደሉ በስተቀር ሌላ ምንም አይነት አስገራሚ ገጠመኝም አልነበረንም::

በመጋቢት 3፣ 2ኛው ብርጌድ፣ ጄኔራል ናፒየር እና ጄኔራል ቻርለስ ስታቨሊ እኛ ያለንበት የአንጣሎ ካምፕ ደረሱ:: በጣም የሚያጓጓ ትዕይንት ነበር:: የ(ትልቅ ትልቁ ጌታ) "ቡራ ቡራ ሳሂብ"፣ ከፈረንጅ ወታደሮች ጋራ መምጣቱ ወሬ ሲሰማ፣ የእንደርታን አውራጃ እንዳለ አነቃቅቶታል:: አንጣሎ የእንደርታ አውራጃ ከተማ ነው:: በሺዎች የሚቆጠሩ፣ እነስ ያለ ልብስ የለበሱ ተዋጊዎች፣ ገላቸው ሙሉ በሙሉ ያልበሰ ሴቶች፣ ጠያይሞች ትንንሽ ልጆች፣ በየመንገዱ ዳር ተጋድመው፣ አዛውንቱ፣ ወጣቱ፣ ወንድና ሴቱ፣ ቄሱም ሆነ ተራው ሰው፣ የማይል በሚሆን ርቀት በመንገዱ ዳርና ዳር ሆነው የትልቁን ጌታ "ሳሂብ" እና የአንግዳ ተቀባዩን መምጣት ይጠብቃሉ::

የሬጅመንቱ የሙዚቃ ባንድ ወደፊት ቀደም ብሎ፣ ለሚመጡት ጓዶቻቸው የእንኳን ደህና መጣችሁ ሙዚቃ ያሰማል::

ጄኔራል ኮሊንግስና ረዳቶቹ፣ ኮሎኔል መርዌዘርና ሌሎችም መኮንኖች፣ ሰር ሮበርት ናፒየርን ለመቀበል እየጋለቡ ወጣ ብለዋል::

በመጨረሻም፣ በጉጉት የሚጠበቀው ጄኔራልና ወታደሮቹ በሙዚቀኞች እየተመሩ መጡ:: ሙዚቀኞቹ፣ አየሩን ሥርአት ባለውና በሌለው ዜማ አደናግረውታል:: የመጀመሪያው ሬጅመንት መታየት ሲጀምር፣ አንጣሎ ያሉት

ወታደሮች ደስታቸውን በሰላምታና በድምፅ ገለጡ፤ ለነሱ ድምፅ ለመመለስ ደግሞ ሬጂመንቱ፣ "ሁዛ!" በማለት፣ በጩኸት ድምፅ አሰማ፡፡ ከኋላ የሚከተለው ጦርም ድምፁ በርቀት እስኪሰማ ድረስ ጩኸቱን አስታጋባ፡፡ ተወላጆቹ ደግሞ፣ በተራቸው፣ ወደራሳቸው እንደበት ቀይረው፣ እልልታውን አቀለጡት፡፡

መጀመሪያ የመጣው የአየርላንዶቹ ሬጅመንት ነው፤ ወታደሮቹ፣ እንደ አነር ፂማቸውን አሳድገው፣ በሞቃታማ ቦታዎች ፀሀይ ፊታቸው ጠቆር ያለ፣ በሙያቸው ልምድ ያላቸው፣ በተለያየ የአየር ጠባይ፣ በህንድ ዘመቻዎች፣ በሂማልያ በረዶዎች፣ በሰንዲ (ፓኪስታን)፣ በወኔ የታገሉ ናቸው፡፡ በላያቸው ላይ የሚውለበለበው የሬጅመንቱ አርማ፣ በአይቤሪያን ሠርጥ ገዳይ ቦታዎች በተደጋጋሚ የተወረወረና የተውለበለበ፣ ለዚህም የዌልንግተንን አከብሮት ያገኘ ነው፡፡

ከነሱ ቀጥሎ፣ 4ኛው ሬጅመንት "የንጉሡ" ጦር መጣ፡፡ እነሱ የያዙት አርማ፣ በክሬሚያ ዘመቻ በእሳትና በአሩር ማዕበል የተብተከተከ ነው፡፡ ከነዚህ ወታደሮች በኋላ የተወላጆቹ ጦር መጣ፤ ይህ የ27ኛው አግረኛ፣ የፑንጃብ ጦር ይባላል፡፡ ሰዎቹም ረዘም ያሉ፣ በሥርአት የተሰለፉ፣ ከህንድ፣ ፑንጃብ ከሚባል ቦታ ነው የመጡት፡፡ የቤሎቺ ሬጅመንት- ቤሎቺዎች አረንጓዴ ጥምጣምና ቀይ ልባስ ነገር ላያቸው ላይ ጠምጥመው ቀይ መስመር ያለው አርንጓዴ ዩኒፎርም ለብሰዋል፡፡ 10ኛው፣ የተወላጆች (ህንድ) አግረኛ በውስጡ ከተለያየ የህንድ ጎሣዎች የተውጣጡ ቆፋሪዎች(መንገድ ሠሪዎች) ያሉበት ነው፡፡ በመጨረሻው ሬጅምንት ካሉት ሰዎች፣ እያንዳንዱ፣ በጦሩ ውስጥ የተሰለፉ ከሰላሳ እስከ አርባ የሚቆጠር ዘመዶች አለው፡፡

ከነሱ በኋላ ደግሞ የፈረሰኛው ክፍል መጣ፣ የሰንዲ ፈረሰኞች፣ ደመቅ ያለ ቀይ ልብሰ ታጥፎ እንደጥምጣም እንገታቸው ላይ ተደርጓል፡፡ ሰዎቹም አረንጓዴ ዩኒፎርም የለበሱ ሲሆን ፈረሶቻቸው ደግሞ አረንጓዴ የኮርቻ እልባሳት ተደርጎባቸዋል፡፡ እያንዳንዱ ሰው አጭር ጥንድ አፈሙዝ ያለው ጠመንጃና የህንድ ጎራዴ ይዟል፡፡

መኮንኖቹ ብርማ ቀለም ያለው ባርኔጣ አድርገዋል፡፡ ከፈረሰኞቹ ኋላ፣ ሰር ሮበርት ናፒየርና ሰር ቻርልስ ስታቬሊ ሥርአት ያለው አለባበስ በለበሱና ባማረ ሁኔታ ፈረስ በሚጋልቡ ረዳቶቻቸው ታጅበው መጡ፡፡ ከወታደራዊ ሁኔታ ለየት የሚያደርግ ከሚገባው ወይም ከመጠን በላይ የሆነ አለባበስም ይታያል፡፡ አንድ ወጣት ጌታ ለምሳሌ፣ ነጭ ጓንትና አርንጓዴ ቬሎ ለብሷል፡፡

የጠቅላይ ዕዝ ጽ/ቤት ሠራተኞችን፣ የ3ኛው ቀላል ፈረሰኛ ኮምፓኒ ይከተላል፤ ፈረሰኞቹ የህንድ ተወላጆች ወታደራዊ ገፅታ ያላቸው ሰዎች

ናቸው፤ መኮንኖቻቸው አንዳንዶቹ ተወላጆች (ህንዶች) ሲሆኑ፣ ልክ ወደ ግርግር ቦታ ሀይለኛ ፈረስ እየጋለበ እንደሚሄድ ሰው፣ በኮርቻቸው ላይ ወደ ላይ ወደ ታች፣ ከፍና ዝቅ እያሉ ፈረሶችን ይጋለባሉ። ሱሪዎቻቸው ከሥር መጠፈሪያ ቀበቶ ስላልነበራቸው፣ ፈርጠም ያሉ ባቶቻቸውን እጋልጠው ያሳያሉ። የነዚህ ወታደሮች ዩኒፎርም እንደ ሰማያዊ ግራጫ መልክ ያለው ሆኖ ነጭ የትከሻ ማንገቻዎችና ነጭ እጅጌዎች አሉበት።

ከነዚህ ኋላ፣ የከባድ መሳሪያው ክፍል ነው የመጣው። ሰድስት የአርምስትሮንግ የሚባለው ከባድ መሳሪያ ባትሪ አለበት፤ ቀጥሎም ዝሆኖችና ጓዝ ተሸካሚው ክፍል ሰባት ማይሎች በሚሆን ርቀት እየተከታተለ ይመጣል። በቅሎ መሪዎች ራሳቸው ብቻ የሠራዊት ያህል ብዛት ነበራቸው።

ከ2ኛው ብርጌድ ጋር የተመደቡ 7ሺ በቅሎዎች ነበሩ፤ ይህ የ2ኛው ብርጌድ፣ የ1ኛው ዲቪዚዮን የሚመራው በጄኔራል ቻርልስ ስታቨሊ ነበር። ለነዚህ በቅሎዎች ደግሞ 3ሺ ሰዎች ያስፈልጉ ነበር። ከዚህ በላይ፣ የካምፕ ሠራተኞች፣ ዝሆን መሪዎች፣ ግመል ነታቾችን ሲጨምር፣ ቁጥሩ በጠቅላላ ወደ እምስት ሺ ሰዎች ከፍ ይላል።

ከነዘህ ሰዎች በተጨማሪ ያገሬው የአቢሲኒያ ሰዎች አሉ። እነሱም፣ ሰፋሪዎች፣ የትምባሆ፣ የዳቦ፣ ገብስ፣ አይብ ሽቃጮች፣ የኮሚሳሪያቱን ፍየሎችና ከብቶች የሚነዱ እረኞችም አሉበት። ከብዛታቸው የተነሳና በቀለምም ለየት ብለው ከመታየታቸው አንፃር ከጠቅላላው መንገደኛ ጎላ ብለው ከሚታዩት ወገን ናቸው። ሌሎች መርሳት የሌለብኝ ሰዎች ደግሞ፣ ብዛት ያላቸው ተሸካሚዎች፣ ልብስ አጣቢዎች፣ ውሀ የሚያመላልሱ፣ ከብቶችን የሚመሩ ሰዎች፣ የዘማቹን ቁጥር እንዲገዝፍ ካደረጉት መሀከል ናቸው። እንዲህ ያለ የተለያየ ገፅታ ያለው ስብጥር በዘመናዊ ጦር ውስጥ ታይቶ አይታወቅም። የዩኒፎርሞቹ ቀለም አይነት፣ የለበሱት ልብስ፣ ምንጣፉ፣ ጥምጣሙ፣ ባርኔጣዎች ደግሞ ውስብስብ ያለ የተለያየ ቀለማት የሚታዩበት ነገር ነው።

የፖላንድ ተወላጆች ከባስታረኒከ ተራራዎች፣ ፂማሞች ጠንካራ ሰዎች ከሳርማቲያን፣ እፍ ከሚያበዙት የፈረንሳይ ተወላጆችና ኮስትር ካሉት ጀርመኖች ጋራ በደስታ ያወራሉ። ጥምጣሙን ያደረገው የቱርክ ተወላጅ፣ ከማይለየው ሱረት ማጨሻው ጋር በመዝናናት አብሮ ይጓዛል፤ የቱርክ ተወላጆች፣ ለእንቅስቃሴ ምንም አይነት ፍላጎት ምልከትም አያሳዩም፤ ጠቆር ያለ መልክ ያላቸው አረቦችም ፍም የመሰለውን ትምባሆ እየሳቡ አብረው ይገኛሉ። የወይራ ቀለም ጉንጮች ያሉት አይሁዳዊም ቢሆን ጥርት ብለው ከሚታዩት አይኖቹ ጋራ፣ በማያውቀው ሀገር፣ ከማያውቃቸው የክሩሴድ ዘማቾች ጋር በሰልፍ የሚከተሉትን በቅሎዎቹን እየመራ ይከተላል። በአእምሮው፣ እንድ ሰፍራ የደበቀው ውድ ንብረት እንዳለና ከአፍሪካ

ሲመለስም የአልማዝ ነጋዴ እንደሚሆን የቀን ህልም እያሰበ ይሆናል:: ለንብጋባ ባህሪ የሚታይባቸው ፋርሶች ወይም ከፔርሽያ የመጡ ጉበሮችም እንድ ሩፒን በትርፍ ሁለት ለማድረግ አጋጣሚ ፍለጋ ላይ ሆነው በቅሎቻቸውን ከሚመሩት አይሁዶች ጋር ጎን ለጎን ይጓዛሉ:: በቅባት የተወለወሉት ከማህራታስ የመጡ ሲኮችም ቢሆኑ ረጋ ካሉት ከደንከን ከመጡ የቁፋሪዎች ዘቦች ጋር የሞቀ ጨዋታ ይዘዋል:: ማቋረጫ ያለው ከማይመስለው ተጓዥ ጋር ደግሞ አስቸጋሪዎቹ ሶማሊዎች ከሶማሊ ላንድ፣ አስቀያሚ መልክ ያላቸው የበርበራ ሰዎች፣ ሁለት ልብ ያላቸው ቤንጋሎች፣ የአውሬ ገፅታ ያላቸው ሾሆች፣ ቀልጣፎቹ ኑብያኖች እና ደፋሮቹ ሀዞራይቶች ይገኙበታል::

በስልፍ የሚወርደው ሰው ምንም የወታደራዊ ስሜት ቢኖረውም በጣም የተደበላለቀ ገፅታ ነበረው:: ነጮች ነበሩ፤ ቀይ፣ ጠየም ያሉ፣ ብጫነት ያላቸው፣ ጥቁሮች፣ ሁሉም ግራ በሚያጋባ ሁኔታ ተቀላቅለው ነበር:: ከሎንደን የመጡ ኮከኒዎች፣ ከአየርላንደ የመጡ ከልትስ፣ አሸዋማ ገፅታ ያለው ፀጉር ያላቸው የስኮትላንድ ሰዎች ከህንዶች ጋር ጎን ለጎን ይጓዛሉ::

የስንቅና ትጥቅ ክፍሉ በቅሎዎች፣ የከፍሉ ማረፊያ ቦታ ላይ ሲደርሱ ጭነታቸው ወረደ:: የጭነት ከብቶችም የተጫኑት ጓዝ በየባለቤቶቻቸው ድንኳን አጠገብ ተራገፈ:: ከዛ በኋላ፣ ከብቶቹ ገንዳዋ ወንዝ አጠገብ ወዳለው በረታቸው ተወሰዱ::

የመድፈኛው ክፍል በግራ በኩል በሚገኝ ጉብታ ቦታ ላይ በመስፈር፣ የብረት መድፎችና ተሸከርካሪዎችን መወልወል፣ ፈረሶችን ውሀ ማጠጣት፣ ከዛም ቀለብ ወይም ምግብ ማከፋፈል ሲጀመር፣ በሌላ አገር እንደሚሆነው ሁሉ፣ ጫጫታ የበዛበትና ግርግር የበዛበት ስፋት ያለው ካምፕ በዚሁ በአፍሪካ አፈር ላይ እየተመሰረተ ነበር::

በስንቅና ትጥቁ ካምፕ ዙሪያ ወዲያውኑ አንግዳ የሆነ ነገር መታየት ጀመረ፤ ከዚህ በፊት ጦሩ ወደ አንጣሎ ሲንቀሳቀስ ተከትዬ አብሬ ብሄድ ኖሮ በተደጋጋሚ ላየው የምችል ሁኔታ ነበር:: ፓረሶች ዶላር የያዙት ከረጢቶችን ይዘው በመውጣት ከሀገሩ ተወላጆች ጋራ መገበያየት ጀመሩ:: እንግሊዞቹ በሊጋስነት ብዙ ብር የሚከፍሉ መሆናቸው ባገሩ ተወላጆች ስለታወቀ፣ በዚህ ግርግር መሀል ትንሽም ቢሆን ሥርአት ያስፈልግ ነበር:: ውድድር ነበር፤ ቀድሞ ስልቻው የያዘውን ገብስ ሚዛኑ ላይ ለመገልበጥና እነዚህን አቢሲኒያውያን በጣም የሚወዱትና ሲያዩት እንኳን አይናቸው በደስታ ወገግ የሚሉባቸውን አዳዲስ የማር ተሬዛ ብሮች በእጅ ለማድረግ ነበር:: ፖሊሶች (ቹፐራዎች)፣ ቀደም ብለው በቦታው ተገኝተው በጉጉት የሚጠብቁትን አቢሲኒያውያን ሥርአት ለማስያዝ ውጤት አልባ የሆነ ጥረት እያደረጉ ነው:: ተወላጆቹ፣ ገብስ፣ ዱቄት፣ አጃ፣ ሌላም አህል፣ ዳቦ፣ ማር፣ የሥር አይነቶች፣

እንጨት፣ ከብት፣ ፍየል፣ በግ፣ በቅሎ፣ አቆማዳና መጫኛዎች ይዘው ይመጣሉ::

በረዳት ሰንቅና ትጥቅ ክፍሉ፣ ለሠራዊቱ የሚሆን ምግብ ለመግዛት ወደ አስራ ሁለት የሚሆኑ ፓረሶች ተቀጥረዋል:: መደነባበር እንዳይፈጠር፣ እያንዳንዳቸው አንዱ ከሌላው በአለር እርምጃዎች ርቀት ተመድበዋል:: ስለዚህ፣ ዳቦ ዱቄቱ ላይ እንዳይወረወር፣ ዶሮና ቅቤ ከዳቦ ጋር እንዳይቀላቀል፣ እንጨቱም ቢሆን ዶሮዎች ላይ እንዳይወረወር ነበር::

እያንዳንዱ ሰው በገበያው ሰዎች ተከቦ፣ እሱና የያዘው የማርተሬዛ ከረጢት ተጋፊ ከሆነ ተመልካች እይታ ተጋርዷል:: ከልጅነታቸው ጀምሮ በማታለልና በማጭበርበር ላደጉ ሰዎች፣ ብር የያዘው ከረጢት የማይቋቋሙት ፈተና ነው የፈጠረው:: ሁኔታውን ለአንዳ አፍታ ላስተዋለ ሰው፣ በመሀል የሚላላኩ የፓረሳውያን ልጆችን ማየት ይችላል:: እነዚህ ልጆች፣ ከሚዋከበው ሰው ወይም ሻጭ ጋር ተደባልቀው ዶላሩን ይቀበሉና፣ ቀስ ብለው ከግርግሩ ወጣ ብለው፣ ከስንቅ ከፍሉ ካምፕ አጠገብ የተወጠሩ ጠቆር ያሉ ድንኳኖች ውስጥ ሲሰወሩ ይታያሉ:: እነዚህ ድንኳኖች ደግሞ እነዚህን ልጆች የቀጠሩ ሰዎች የሚኖሩበት ነው:: በአንድ ቀን እንደነዚህ አይነቶች የመሀል ገብ ሥራዎች በብዛት ይከናወናሉ፤ ምናልባትም፣ እያንዳንዳቸው ሻጮች ከሰባ አምስት እስከ መቶ ዶላሮች ያግበሰብሳሉ:: በጣም የሚገርመው፣ አንድም ፓረሲ በሌብነት ተከሶ ቀርቦ አያውቅም:: የሚሠሩት ሥራ ታላቅ አስተዋፅኦ ስላለው፣ እነሱ ላይ ከረር ያለ እርምጃ መውሰዱ ለፖለቲካው የሚበጅም አልነበረም:: ቢሆንም ከነዚህ ጎሰኞች ጋር ያለተነካኩ ውለታ የሌለባቸው ጥቂት መኮንኖች ብቻ ነው የነበሩ::

አነስ ያሉ የወረቀት ገንዘቦች፣ ያለነዚህ ሰዎች ርዳታ ወደ ጥሬ ገንዘብ መቀየር አይቻልም:: የወታደራዊ መኮንኖች ደግሞ ከሌላው ሰው በበለጠ ሁኔታ ገንዘባቸውን እንደልብ ለማውጣት ነፃ ስለሆኑ፣ በዚህ ዋጋ በናረበት በአቢሲኒያ፣ እንደዚህ አይነቱ ወደ ጥሬ ገንዘብ መቀየር አስፈላጊና በብዛትም የሚደረግ ነገር ነበር:: ከጦሩ ካዝና መጠቀም ያልተለመደ ሥርአት ስለሚሆን፤ መኮንኖቹ የፓረሲዎችን ግብረገብ የጎደለው ሥራ ለማጣራት ከመንቀሳቀስ ይልቅ ለህንድ ደላሎች ከፍ ያለ ቅናሽ መክፈሉን ይመርጣሉ::

ከላይ እንደገለፅኩት፣ የማጓጓዣ ከብቶች ጭነታቸው ከወረደ በኋላ ወንዙ አጠገብ ወዳለው ካምፕ ተወስደዋል:: የማጓጓዣ ክፍሉን በደንብ ለመረዳት፣ በሚቀጥሉት ገፆች ቃሉ ተደጋግሞ ለለሚመጣ፣ በሚቀጥለው ሁኔታ አገልፀዋለሁ::



የበሎቺዎች ሬጅመንት

ወደ አቢሲኒያ የሚመጣው አጠቃላዩ የማጓጓዣ መስመር በየካቲት 14፣ 1868 ከቦምቤይ ነበር የተፈጠረው:: ነገር ግን፣ ይህ መስመር ከዚህ ቀደም በጥቅምት ወር ለአፍሪካ ጉዞ ተዘጋጅተው ከነበሩ ከሁለት የፑንጃብ የማጓጓዣ ክፍሎች ነው የተመሠረተው ማለት ይቻላል::

የደጋማው የማጓጓዣ መስመር የተደራጀው ለደጋማው የአቢሲኒያ ክፍል ነው፤ የዚህ ክፈሉ፣ በሰር ቻርለስ ስታቨሊ በሚመራው አሁን ወደመቅደላ በመገስገስ ላይ ላሉት የ1ኛው ዲቪዚዮን 1ኛውና 2ኛው ብርጌዶች ጓዝና ምግብ ያጓጓዛል፤ የቆላማው የማጓጓዣ መስመር ግን በሰናፌና ዙላ መሀል አገልግሎት ለመሥጠት የተወሰነ ነበር::

የደጋው የማጓጓዣ መስመር፣ እያንዳንዳቸው 2ሺ በቅሎዎች ባሉባቸው አራት ክፍሎች የተከፈለ ነበር፤ እያንዳንዱ ክፍል ደግሞ 150 ወታደሮች ሲኖሩበት፣ የክፍል መጠንና አደረጃጀት ደግሞ እንደሚከተለው ነበር::

1 ካፒቴን

3 ዝቅተኛ መኮንኖች

4 አውሮፓውያን ተቆጣጣሪዎች (ከብሪታንያ ሬጅመንት የተመረጡ)

20 ጃማዳር ወይም ሻምበል ባሻዎች

80 ዱፋዳሮች ወይም ሃምሳ አለቃዎች

667 በቅሎ መሪዎች

2 ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው ናልባንዶች ወይም የፈረስ ጫማ ሰሪዎች

10 ምክትል ደረጃ ያላቸው ፈረስ ተንከባካቢዎች

1 የህንድ ተወላጅ አንጥረኛ አለቃ

10 ረዳት አንጥረኞች

10 ውሀ አመላላሽ ከብቶችን የሚቆጣጠሩ

2 ገመድ ሠሪዎች

1 የህንድ ተወላጅ የከብት ሀኪም

1 የህንድ ተወላጅ ፀሀፊ

ዘመቻው ሲጀመር፣ አንድ ሰው ሁለት በቅሎዎች ብቻ ነበር የሚቆጣጠረው፤ ሁለቱን ብቻ መንከባከብ እንጂ ሌላ ስራም አልነበረውም:: ጋጣ፣ ውሃ ማጠጣትና ሌሎች ሥራዎችም ከቤንጋል ፈረሰኛ ሬጀመንት ቀን ተቀን ሥራ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ነበር የሚሠራው:: እነዚህ በቅሎ መሪዎች ትምህርት የተሠጣቸው በመሆኑ ስራቸውን ጠበቅ ባለ ሥነ ሥርአት በሚገባ ነበር የሚያከናውኑት:: ሻምበል ባሻዎቹ፣ በነሱ ምድብ ያለውን የወታደር ስም ዝርዝርና የሚከፈለውን ክፍያ በፋርስ ቋንቋ ነበር የሚመዘግቡት:: የእያንዳንዱ

ሰው ሙሉ ዝርዝር በፋርስ ቋንቋ በፀሀፊዎች ተመዝግቧል፤ የክፍያ ሂሳብ ደግሞ፣ በእንግሊዝኛ በካፒቴኑ እጅ ይቀመጣል::

የጉንጃቡን የማጓጓዣ መስመር የሚያዙት መኮንኖች ያልተገደበ ሥልጣን አላቸው፤ በዚህም ሰዎችን ሰውነት ላይ ቅጣት ማስፈፀም ብቻ ሳይሆን ለሁለት አመታት የማሠር መብት አላቸው:: ሁሉም በምክትል ዳይሬክተሩ ትዛዝ ስር ነው፤ ምክትል ዳይሬክተሩ የጠቅላይ ዕዝ ቢሮ አባል ሆኖ፣ ቀጥታ ለረዳት የትጥቅና ስንቅ ሀላፊው ክፍል ሪፖርት ያደርጋል:: ለዚህም የስታፍ መኮንንና፣ በየቦታው እየተዘዋወረ የሚያየውን ወይም የዘገበውን ሁሉ ነገር ለሱ ሪፖርት በሚያደርግ ተቆጣጣሪ ይታገዛል:: የማጓጓዣ መስመሩ በአዲግራትና በመቅደላ መሀከል ያጓጉዛል:: ዋና ሥራውም፣ ጓዞችን፣ ጥይቶች፣ የሆስፒታል መገልገያዎችን እና ለጦሩ ለአንድ ወር የሚሆነውን ስንቅ ማቀበል ነው:: በመሀል በሚገኙ ተለቅ ያሉ ጣቢያዎች ላይ የስታፍ መኮንን በቋሚነት ተመድቦ የጓዙ ሀላፊ ከሆነው መኮንን የሚደርሰውን ሪፖርት በመቀበል ለጠቅላይ ዕዙ ጽ/ቤት ያስተላልፋል:: በነዚህ መሀል ቦታዎች ላይ ተጠባባቂ የጭነት ከብቶች ተዘጋጅተው ይጠብቃሉ፤ ይህም የታመሙ ወይም የደከሙ የጭነት ከብቶችን ለመተካት ነው:: በቅሎዎቹ፣ ከስፔይን፣ ከግብፅ፣ ከህንድ፣ ከፔርሺያ እና ከአቢሲኒያ እየተገዙ ሥራ ላይ ይውላሉ::

የስፔይን በቅሎዎች ገዘፍ ያሉ ጥሩ ዝርያ የሌላቸው ናቸው:: እንዳየሁት ከሆነ፣ በተፈጥሯቸው ደከም ያሉ ሆነው ተለዋዋጭ የአየር ፀባዩን የሚቋቋሙ አልነበሩም:: በብዛት የሚሰቃዩት በነበራቸው የመመገብ ፍላጎት ምክንያት ነበር፤ በተለይም ሳሩ ቢኖርም በበቂ መጠን ስለማያገኙ ነበር:: የተገኘው ሳር ደግሞ የደረቀና ሸካራ በመሆኑ አልወደዱትም:: ምንም እንኳን አርፈውና እንደልባቸው የሚግጡት ሳር በመሀል ጣቢያዎች ቢገኝም፣ አንድ ጊዜ ከደከሙ መልሶ ለማጠንከር አስቸጋሪ ነበር:: መጠነኛ የሆኑት ጥሩ ዝርያ ያላቸው የስፔይን በቅሎዎች ግን ደህና ምላሽ ያሳያሉ:: የፔርሺያ፣ የህንድና የግብፅ በቅሎዎች በተቃራኒው ችግር ቻይ፣ መጠነኛ አህል የሚበቃቸው፣ ያገኙትን የሳር አይነት የሚበሉና በዛም የሚዳብሩ ነበሩ::

የአቢሲኒያ በቅሎዎች ችግር የሚቋቋሙ አልነበሩም፤ ሲገዙ በጥሩ ሁኔታ የነበሩት እንኳን፣ ከሌሎቹ በተለየ ሁኔታ በብዛት ከአገልግሎት ውጭ ነበር የሚሆኑት:: በመጋቢት 1፣ 5412 ከብቶች በደጋው የማጓጓዣ መስመር ውስጥ ነበሩ ከነዚህ መሀል 1002 የሚሆኑት በሽተኞች ነበሩ::

በሚያዝያ 1፣ 6691 ከብቶች ነበሩ፤ ከነዚህ ውስጥ 1002 በሽተኞች ነበሩ:: በግንቦት 1፣ ከ7960 ከብቶች መሀል 1944 በሽተኞች ነበሩ:: ከመጋቢት 1 ጀምሮ በደጋማው ሀገር 2720 ከብቶች ሲገዙ፣ ከቆላማው፣ 1740 የሚሆኑት ወደ ደጋማው ቦታ እንዲመጡ ተደርጓል:: ከዚያ ጊዜም ጀምሮ

በመንገድ ላይ 449 ከብቶች ሲጠፉ፣ 1257 የሚሆኑት ወደ ቆላማው የማገገሚያ ቦታ ወደ ቁማይሌ ተልከዋል፡፡ እነሱም እንደማይመለሱ ተሰርዘው ነው፤ 309 ከብቶች በደጋማው ማገገሚያ ጣቢያ ተገድለዋል ወይም ሞተዋል፡፡ 2418 የሚሆኑት በህክምና አገግመው ተመልሰው ወደ ሥራ ተልከዋል፡፡ በቅሎዎቹም ፋታ ሳያገኙ ከመርከብ እንደወረዱ ነበር አገልግሎት ላይ የዋሉት፡፡

ሠራዊቱን ተከትለው ከመጡ ሰዎች መሀከል ጉልህ የሆነ የሥራ ባህሪ ልዩነት አለ፡፡ ከነዚህ መሀል ጦሩን ተከትለው፣ ከህንድ፣ ራውል፣ ፒንዲ ተነስቶ እስከ ፐርሺያ ሰርጥ ከራቺ ድረስ ለ፲፫ ማይሎች መንገድ በመጓዝ ልምድ ያካበቱት ሰዎች፣ የጭነት ከብቶቻቸውን በደንብ ነበር የያዙት፡፡ በተለይም ከዶክተር ሀለን በኩል የሚመጣውን ችግርና ጭቅጭቅ ችለው ነው፡፡ ሌሎቹ ከግብፅ፣ እስከንድርያና ካይሮ የተመረጡ ተራ ሰዎች፣ በመቶዎች ቁጥር ሆነው ለሚፈለገው አገልግሎት የመጡት፣ የሚቆጣጠሯቸውን እንስሶች ለሚያሳዝን አደጋ ነው የዳረጓቸው፡፡ በጥባጭና ተተናኳይ ከመሆናቸው በተጨማሪ፣ አስቸጋሪ ዳገትና ተራራዎችን የመውጣት ችሎታም አልነበራቸውም፡፡ ይህም ከዚህ በፊት በነበራቸው የሰንፍና ባህሪ ምክንያት ነው፡፡

አገልግሎት ላይ የዋሉት ኮርቻዎች የተለያዩ አይነት ነው የነበሩት፡፡ የቦምቤይ ፓድ፣ አስቸጋሪው የቱርኮች፣ አታጎና መከማሆን የሚባሉ የእንግሊዝ ኮርቻዎች ነበሩ፡፡

የኦታጎው ኮርቻ፣ በኔ አስተያየት፣ ከተሠሩት ሁሉ በጣም ጥሩው ነው፡፡ ከጠንካራ፣ ከእንግሊዝ አገር ቆዳ የተሠራ ነው፡፡ ጎንና ጎኑም ከዚሁ ከእንግሊዝ አገር ቆዳ የተሠራ ሆኖ፣ የከብቱ ጎን ላይ ከሚያርፉት ከአራት ማዕዘን ትራሶች ጋር የተሰፋ ነው፡፡ እነዚህ ደግሞ፣ በቆዳ ከተሸፈኑ፣ ከከብቱ አከርካሪ ሶስት ኢንች ከፍ ፍሎ ከሚገኝ ጎበጥ ያለ ጠንካራ የብረት ደጋን ጋር ይገናኛሉ፡፡ በሁለት ጎን ሁለት መንጠቆዎች አሉ፤ እነሱም የሚንጠለጠውን እቃ አስረው መያዝ የሚችሉ ጠንካራ ቀበቶዎች በተለያየ ርዝመት አሉባቸው፡፡ ክብደቱ ወደ 28 ፓውንዶች ይሆናል፡፡ መከ ማሆን የሚባለው፣ ጥቅጥቅ ያለ ኮርቻ ሲሆን የ66 ፓውንድ ክብደቱ ግን ለአግልግሎት እንዳይውል ያደርገዋል፡፡

ስለ እንስሳቱ ህመምና ሞት የጠየቅሁት፣ ከ፲ኛው ዲቢዚዮን ጋር የተመደበው የከብት ሀኪም፣ ለእንስሳቱ በብዛት መታመምና መሞት ዋናው ምክንያት፣ "በከፍታ ቦታ ላይ ከባድ ሥራ፤ ዕረፍት እያስፈለጋቸው ግን ያለማቋረጥ እንዲሰሩ መደረግ፤ በቂ ምግብ አለመኖርና፣ የሳሩ አይነት ጥራት የሌለው በመሆኑ፤ ጊዜ ጠብቆ አለመመገብ፤ በመጥፎ ኮርቻ ምክንያት መቁሰል፤ የቆሰለውንም በጊዜ ማከምና ማሳረፍ አለመቻል፤ የከብት ጫኞቹ ግድየለሽ ኮርቻና ጭነት አጫጫን ነው፡፡" በማለት ተናገረ፡፡ በቅሎ ጫኞቹ

ከብቶች ከሀገሩ ተወላጆች መግዛት ስለሚችሉ ነው፤ ስለዚህ በወቅቱ ለአገልግሎት የሚውሉ ስድስት መቶ ጋሪዎች ነበራቸው::

የከብት ሀኪሞች ክፍል፣ ለጠቅላይ ዕዝ ቢሮው የጭንቀት መንሥኤ ነው የነበረው:: ከቦምቤይ ሲነሳ፣ ይህ ክፍል በሚያሳዝን ሁኔታ የተሟላ አልነበረም:: ያም ሆኖ፣ ከጣልያንና ከፈረንሳይ ከብት መሪዎች መሀከል ከስምንት እስከ አስር የሚሆኑ፣ የከብት ህክምና የመጀመሪያ ደረጃ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ተሰበሰቡ:: ይህ በተራው ለሰርጀኖቹ ትልቅ እርዳታ ነው የሠጠው፤ አብዛኞቹ ወጣት የነበሩና በቅርቡ ወታደራዊ አገልግሎት የገቡ ነበሩ፤ ቢሆንም በነበራቸው ከፍተኛ ጉልበት እና ለመሥራት በነበራቸው ፈቃደኝነት መልካም አገልግሎት ነበር የሠጡት:: እነዚህ መኮንኖች በቀጥታ በሰርጀን ላምብ ስር ነበሩ፤ የሠርጀኑ ሀላፊነት ደግሞ ታለቅ ነበረ፤ በመጀመሪያዎቹ አካባቢ፣ ለ30ሺ እንስሳት ሃላፊ ሲሆን እየቆየ ደግሞ ቁጥሩ ወደ 53ሺ ከፍ ብሎ ነበር:: እናም ከአስር ሰርጀኖች ብቻ ነበር ርዳታ ማግኘት የሚችለው:: እነዚህ ሰዎች ደግሞ በነበረው ሁኔታ ነው መሥራት የሚችሉት፤ በጣም ያልተለመደ ሥራም ነበር:: ራሳቸው መድሀኒቶችን በየጊዜው መቀመም ነበረባቸው፤ ከዛም መድሀኒቶቸን መስጠት፤ የታመሙ ከብቶች ማጠብና ቁስላቸውን ማከም፤ ስለዚህ ለራሳቸውም ረዳት ያስፈልጋቸው ነበር::

ለጉዞው የሚሆኑ በቂ ቁጥር ያላቸው ከብቶችን ማቅረብ ብዙ ጉልበትና ወጭ ይጠይቃል:: በተለያዩ ቦታዎች ያሉ የእንግሊዝ ቆንስላዎች፣ ማላጋ አሊካት፣ ካዲዝ፣ ባርሰሎና፣ ጀኖአ፣ ትሪፖሊ፣ ቤይሩት፣ ኮንስታንቲኖፕል፣ ሰሜርና፣ ጂብራልታር እና በማልታ የሚገኙ፣ በቅሎዎች እንዲያዘጋጁ ትዛዝ ተላለፈላቸው:: መኮንኖቹም ከሰርጀኑ ጋር በመሆን ተልከው፣ ወደከብት ማጎሪያው ከሚላኩት ውስጥ፣ ለሥራ የሚስማሙ የጋማ ከብቶች መመርመርና መምረጥ ነበረባቸው:: በእንግሊዝ ውስብስብ ባለው የዲፓርትመንቶች መንግሥት መሠረት፣ ከሚያስፈልገው በላይ ቁጥራቸው በርከት ያሉ መኮንኖች ያስፈልጉ ነበር፤ በዚህ ምክንያት ሁሉም ነገር ውድ ነው የሆነው::

በተቻለ መጠን፣ ወደፊት የሚላከውን የጓዝ መጠን ለማፋጠንና በዝቅተኛው ቦታ ያለውን የማጓጓዣ መስመር ለማገዝ፣ ከዙላ እስከ ቁማይሌ አጠር ያለ የባቡር ሀዲድ ተሠራ:: ይህ በተራው፣ በዙላ ባህር ዳርቻ ጋማ ከብቶች ሊቆዩ የሚችሉበትን ሁኔታ መከላከል አስችሏል፤ እለበለዚያ ቦታው ልክ እንደደረሱ ለከብቶቹ የሕየወት ማለፍ ምክንያት ነው የሆነው:: የቀንድ ከብት ጋሪዎች በሞቃታማው አሸዋ ሊጎተቱ የነበረውን ሁኔታም ቀይሮታል::

መርከቦቹ የጫኑትን ጓዝ ወደቡ ላይ እንዳራገፉ ወድያውኑ፣ ኩሊዎች የባቡር ፉርጎዎች ላይ ከጫኑ በኋላ፣ ባቡሩ፣ የአስራ ሁለት ኪሎሜትር ርቀት፣ ወደ ቁማይሌ ጣቢያ ይወሽዳል:: ስለዚህ ቁማይሌ ሰፋት ያለው የጓዝ

መከማቻ ነው የሆነው። የነበረው አሰራር፣ ሁለት ወይም ሶስት መቶ ፉርጎዎች በአንድ ጊዜ እንዲጫኑ ሆኖ ነው፤ ከዚያ በኋላ ወደ ሰናፌ፣ ከዛም ወደ አዲግራት መንገዱ ጥሩ ነበር። ሀዲዱን ለመስራት የተጠቀሙባቸው ብረቶች ቀላል ነው የነበሩት፤ ማለትም 30 ፓውንድ በያርድ፣ ወይም 25 ቶን በማይል ነበር። የሚዘረጉት ሀዲድ መስመሮች ደግሞ 6 ጫማ ርዝመትና በውፍረት እንደ እራተኛ ኪዮቢክ በዳያሜትር ነበር። የነበሩት ሶስት ባቡሮች በጣም ደካማና የሚንገጫገጩ ነበሩ፤ ቢሆንም ለተመደቡበት ሥራ የተመቹ ነበሩ። በዚህ ሁኔታም፣ በአንድ ሰአት ውስጥ፣ ከአስራ ሁለት እስከ አስራ አምስት የሚሆኑ የጭነት ፉርጎዎች ከዙላ ወደ ቁማይሌ መጓተት ይችላሉ።

ለሁሉም፣ ለጄኔራል መኮንኖችና ለሌሎችም የመካዝን ተቆጣጣሪዎች ጠቃሚ ሆኖ የተገኘው ቴሌግራፉ ነበር። የአንድ ነገር እጥረት ካለ፣ ቡቴሌግራፍ፣ ሰናፌ ወይም ቁማይሌ ላለው ተቆጣጣሪ መልከት ይላክና የጎደለው ነገር በሁለት ወይም በሶስት ቀናቶች ውስጥ ይላካል። እንዲሁም፣ ቀጥታ ከግንባሩ የሚገኘው ዜና፣ መልከት ለሚያመላልሰው መርከብ እነስሊ ወደብን ከመልቀቁ በፊት ሲደርስ ይችላል።

የአቢሲኒያ ዘመቻ ሲደራጅ፣ የታለመው የቴሌግራም መስመር፣ በቀይ ባህር ዳርቻ ከሱአኪም ተነስቶ በግብፅ ደንበር አድርጎ እስከ እነስሊ ወሽመጥ እንዲዘረጋ ነው። ከሱአኪም ወደ ካይሮም መስመር መዘርጋት ይቻላል፤ ያም ከሱዌዝ፣ ካይሮና እለከሳንድሪያ መስመር ጋር ያገናኝዋል። ነገር ግን ይህንን ለመዘርጋት የሚያስፈልገው የግንባታ ሥራ ከብደት፣ የእንግሊዝን መንግሥት ሀሳቡን እንዲተው አድርጎታል።

ከአንጣሎ ወደ መቅደላ፣ እስራ ሰባት ቀናት ይወስዳል፤ ያም በቀን ሁለት ማይሎች ብቻ መጓዝ ከተቻለ ነው። ጄኔራል ናፒየር፣ በሆነ ምክንያት ብቻ፣ መቅደላ መድረስ የሚችለው በሰላሳ ቀናት እንደሚሆን አምኗል። ለአስር ሺ ሰዎች፣ ከብት ጫኞችና ካምፕ ሠራተኞችን ጨምሮ፣ ለሰላሳ ቀናት የሚሆን ቀለብ ለማጓጓዝ፣ እያንዳንዱ የጭነት ከብት 150 ፓውንዶች ቢሸከም፣ በጠቃላይ 4ሺ የሚሆኑ የጭነት ከብቶች ያስፈልጋሉ። ጓዝ፣ ድንኳኖች፣ ርኪቶች፣ የተራራ ከባድ መሳሪያዎችና ጥይቶችን ለማጓጓዝ ከዚህ ቁጥር በላይ እንስሶች ያስፈልጋሉ።

በምንም መንገድ ቢሆን ለጦሩ ቀለብ የሚሆነውን በሙሉ ከሀገሩ መሰብሰብ ይቻላል ብሎ ማመኑ ጥሩ አይሆንም። የአስራ አምስት ቀናት የሚሆን ቀለብ በእጃችን ከያዝን፣ ካለፈው ባገኘነው ልምድ በመነሳት፣ ረሃብን ማስወገድ እንችላለን። በየቦታው መቆም ተደጋጋሚ ሊሆን ስለሚችል የአስራ ሰባት ቀኑ መንገድ ወደ ሁለት ወራትም ሊራዘም ይችላል። ብልጭልጭ የሚለውን ከብር የተሰራውን ጠገራ ብር ካዩ፣ የተወሰነ መጠን ዶቄትና ዳቦ

ከሀገሩ ሰዎች ሊጠበቅ ይችላል፡፡ አንባቢ መረዳት እንደሚችለው፣ ልምድ ባለው ጄኔራል ናፒየር ብልሀነት ረጋ ባለ አርቆ ማሰብ ችሎታው ያልተጠበቁ ድንገተኛ ሁኔታዎች ሊጠበቅ ይችላል፡፡ በዚህ ብዙ ሁኔታዎች ባሉበት ጉዞ የሆነው ነገር በሚቀጥሉት ገፆች ይገለጣል፡፡

የጄኔራል ናፒየር ስሌት ምን ያህል ትክክል እንደሆነ ወይም ምን ያህል እንደተሳሳተም ይገለጣል፡፡ በያዘው ወደ አንድ መቶ ሺ ዶላሮች፣ ሰር ሮበርት ናፒየር ብዙ ነገሮች ማድረግ ይችላል፡፡ ለአለቆች መደለያ፣ ለመንደር ሀላፊዎች ስጦታ መስጠት አስፈላጊ ነበር፤ በዚህም አስፈላጊ የሆኑ፣ ለቀለብ የሚሆኑ ሁሉም ነገሮችን ማግኘት መቻሉን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ የነበረን ገንዘብ ዶላሩ ብቻ ነበር፡፡

በአቢሲኒያ የነበረው መገበያያ 8 ኢንች ርዝመት፣ አንድ ኢንች ስፋትና አንድ ኢንች ውፍረት ያለው አሞሌ ጨው ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ሀሸድ ከሚባል ቦታ ነበር የሚቆፈረው፡፡ በ1780 ከተሠራው ከአውስትሪያው ዶላር ውጭ፣ ሌላ የመገበያያ ገንዘብ ተቀባይነት የለውም፡፡ ከዛን ጊዜ ጀምሮ፣ ዶላሩ ያገሩን የወርቅ ገንዘብ ተክቷል፡፡

ጄኔራል ናፒየር፣ ሩፒ[86] ወይም ሽልንግን ለሀገሩ ለማስተዋወቅ በጣም ጥሮ ነበር፤ ለመስፍኑ ካሳም ደብዳቤ ፅፎለት ነበር፤ ነገር ግን ተቀባይነት የማይኖረው መሆኑ ወዲያው ነው የታወቀው፡፡ በዚህ ረገድ ተሳክቶለት ቢሆን ኖሮ የዕቃዎች ዋጋ አሁን ከተከፈለው በግማሽ ይቀንስ ነበር፡፡

ያገሩ ተወላጆች ለዶላሩ ከፍተኛ ፍላጎት ቢኖራቸውም፣ ጥንቃቄ በማድረግ ገንዘቡ ላይ ያሉት የመለያ ምልክቶች መታየት የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይፈልጋሉ፤ አለዚያ ሁሉንም አይቀበሉም፡፡ ምልክቶቹ ደግሞ፣ የንግሥት ማሪያ ተሪዛ ምስል፣ ጭንቅላቷ ላያ ያሉት አንቁዎችና፣ በትከሻዋ ላይ ያለ አንቁና ገንዘቡ ላይ የታተመው S.F የሚል ፅሁፍ ናቸው፡፡ ለለዚህ ሁሉም ገንዘቦች የውነተኛው መሆን እንዳለባቸው በጣም አስፈላጊ ነበር፡፡ ያን አይነቱ ዶላር ደግሞ በበቂ መጠን ስላልነበረ አዲስ መሠራት ነበረበት፤ ስለዚህ፣ ጊዜው ያለፈ ይህ ገንዘብ፣ 500 ሺ የሚሆን በአውስትሪያ ቪየና በሚገኘው ኢምፔሪያል ገንዘብ መሥሪያ ቦታ ለአቢሲኒያ ዘመቻ ተብሎ በአጣዳፊ ነበር የተሠራው፡፡

ሠራዊቱ አንጣሎ በደረሰ በመጀመሪያው ቀን ጠዋት፣ ጠቅላይ አዛዡን ማየት እንዳለብኝ ወሰንኩ፤ በሁሉም አገሮች ደንብ መሠረት፣ በሠራዊቱ ውስጥ የሚገኝ ማንም ሲቪል፣ ዋና ቢሮ ድረስ በመሄድ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

---

[86] ሩፒ የህንድ መገበያያ ገንዘብ ሲሆን፣ ሽልንግ ደግሞ የእንግሊዞች ነበር




*ማርያ ተሬዛ፣ (ማር ተሬዛ)ጠገራ ብር*

እስካሁን ድረስ ግን፣ ጄኔራሉ ልክ እንደ ጃፓን ሚካዶ[87] ወይም እንደቲቤት ላማ ከኔ የተሰወረ ነበር። በነበረው ከፍተኛ ሥልጣን ምክንያት በጣም የሚከበር ስለሆነ፣ ሊጣስ በማይቻል የወታደሮች ዘብ እጥር ተከቧል። ከነዚህ በተጨማሪ፣ የሚያንፀባርቅ የወታደር ዩኒፎርም የለበሱ ከፍተኛ ማዕረግ ያላቸው መኮንኖችም አሉ።

“ጄኔራሉን ማየት እችላለሁ?” በማለት፣ አንድ መልከመልካም ፣ ጠንከር ያለ ሰውነት ያለው የካምፑን ረዳት ካፒቴን ኤስን ጠየቅሁ።

“የምን ጄኔራል?” መልሶ ጠየቀኝ።

“ሰር ሮበርት ናፒየርን፣ ሰር፣” ብዬ በደፈናው መለስኩኝ።

“እሃ! የተከበሩት ሰር ሮበርት ናፒየርን ማለትህ ነው?” አለ፤ በመጠኑ ቅንድቦቹን ወደላይ ከፍ አድርጎ።

“በርግጥ፣ ሰር፣” ብዬ መለስኩ፣ “አዎ፣ የተከበሩ ሰር ሮበርት ናፒየር፣ ሌፍተናንት ጄኔራል፣ የአቢሲኒያ ዘመቻ ሠራዊት ጠቅላይ ጦር አዛዥ፣ አሁን በአቢሲኒያ የሚገኙትን”

“አሁን ልታየው አትችልም” አለ፤ ፈዘዝ ያለ የፈገግታ መልክ በፊቱ ላይ እያሳየ፤ “ቁርስ ላይ ነው።”

87 የጃፓን ንጉሠ ነገሥት

ማምሻውኑ እንደገና ሞከርኩ፤ አሁን ደግሞ፣ እጅ ለመንሳት ከመጡ ከተወሰኑ የአገሩ ባላባቶች ጋር ነው::

በነጋታው ጠዋት እንደገና ሞከርኩ፤ እለመታደል ሆኖ፣ ዛሬም ቁርስ ላይ ነው:: ከሰአት በኋላ ስሞክር፣ አንቅልፍ ላይ ነው::

በሶስተኛው ቀን፣ ጠዋት ሶስት ሰአት ላይ እንደገና ሞከርኩ፣ ነገር ግን አዛገቡ ማታ ሲሰራ ስላደረ አንቅልፍ እንደተኛ ነው::

ከሰአት በኋላ፣ ከቀኑ ስምንት ሰአት ላይ እንደገና ጠቅላይ ቢሮ ስሄድ፣ መከሰስ እየበላ ነው::

በአራተኛው ጠዋት፣ ከጠዋቱ አምስት ሰአት ሊሆን፣ የካፒቴን ኤስ ድንኳን ለሰባተኛ ጊዜ ቀረብኩኝ፤ ሰር ሮበርትን ለማየት ፈቃድ እንዲሠጠኝ ነበር::

"የተከበረው ሰር ሮበርት ናፒየር ሥራ ላይ ነው?" ብዬ በትህትና ጠየቅሁ::

" አሃ! ስምህን ማን ልበል?" ካፒቴኑ ጠየቀ::

" ካርዴ ይኸውና፣ ሰር!"

"ህም! አዎ፣ ሚስተር ስታንሊ፣ የኒውዮርክ ሄራልድ ዘጋቢ:: መልካም ፈቃድህ ከሆነና ብትቀመጥ፣ ሄጄ፣ ሰር ሮበርትን አነግራለሁ::"

ከተቀመጥኩ በኋላ፣ ጠቅላይ አዛገቡ በምን አይነት ሁኔታ እንደሚቀበለኝ ማሰብ ጀመርኩ::

"ሰር ሮበርት ናፒየር ሊያይህ ፈቃደኛ ነው፣ ሰር!" አለ ካፒቴኑ::

ይህንን መኮንን እየተከተልኩ፣ እንደ እንግዳ መቀበያ ከፍል ወደሆነ ድንኳን ውስጥ ገባሁ:: ድንኳኑ ብጫ ከጥጥ የተሠራ ከፈፍ ያለው ሲሆን፣ ወለሉ ላይ የፔርሽያ ምንጣፍ ተዘርግቶበታል፤ ይህ ከፍል፣ ከውሥጠኛው ጋር ከሀር በተሠራ መጋረጃ ተከልሏል:: ጋዜጣና ዶሴዎች በተደረደሩበት ጠረጴዛ አጠገብ፣ ያልተቆለፈ ዩኒፎርም የለበሰ ሰው ተቀምጧል፤ ግራጫ ቀለም ያለው የጭንቅላት ፀጉርና ፂም ሲኖረው፣ በርጋታና በፀጥታ፣ ልክ አርሻውን ሲያይ ውሎ የሚጠበቀው ምርት ጥሩ በመሆኑ ደስተኛ የሆነ ገበሬ አይነት ነው::

"ሚስተር ስታንሊ፣ ሰር ሮበርት" በማለት ካፒቴኑ አስተዋወቀን::

በዚህ ድምፅ፣ ረጋ ብሎ የተቀመጠው ትልቅ ሰው ከመቀመጫው ተነስቶ ትውውቁን በማፅደቅ፣ ወዳጅነት በሚያሳይ ሁኔታ ጭንቅላቱን ጎንበስ በማድረግ በእጁ በማሳየት እንድቀመጥ ጋበዘኝ::

"ፍቀድልኝና፣ ሰር ሮበርት፣ ካንተ ጋር እንድተዋወቅ የያዝኳቸውን ደብዳቤዎች እንድትመለከታቸው ላሳይህ::"

"አመሰግናለሁ፣ ጀኔራል፡፡ መልካም ፈቃድህ ሆኖ ልጠይቅህ የምመኘው ነገር ደግሞ፣ ፖለቲካውን በሚመለከት የመረጃ ሥራዎችን ጠቅለል ያለ ነገር ማየት እንድችልና፣ ለሌሎች መገናኛ መላክ ይቻላል ብለህ የሚስማማ ነው የምትለውን ነገር ማካፈል እንድችል፣ ምክንያቱም ከኒው ዮርክ ሄራልድ፣ አንተ የምትሠጠኝን ዜና ወይም እኔ የማገኘውን እንዳስተላልፍ ይጠበቅብኛል፡፡"

"በርግጥ፣ ደስ ይለኛል፤ ረዳት ጀኔራሉ ወይም የፖለቲካ ፀሐፊው ለሌሎቹ ዘጋቢዎች የሚሠጡትን መረጃ ማየት ትችላለህ፡፡"

ከመለያየታችን በፊት፣ ጀኔራሉ በደግነት፣ የያዝኩት ገንዘብ ካነሰኝ፣ በድራፍት መልክ አስፈላጊ የሚሆን ገንዘብ ለመሥጠት እጁን ዘረጋልኝ እናም ማምሻውን ለእራት ጋበዘኝ፡፡

ልክ ከምሽቱ አንድ ሰአት ላይ፣ በሰር ሮበርት ናፒየር የተጋበዙ እንግዶች በሙሉ በካምፑ ውስጥ በሚገኝ ረዥም ጠረጴዛ ዙሪያ ተሰብሰበዋል፡፡ ጠረጴዛው ላይ፣ ሰሀኖች፣ መጠጫዎች፣ ብርጭቆዎች፣ የወይን መያዣ ጠርሙሶች እና የማጣቀሻ ምግብ መያዣዎች ሞልተውበታል፡፡ ስመልፈንገስም የድግሱ አባል ነበር፡፡ በሚደነቅ ሁኔታ በብዛት ከየሀገሩ የሰበሰባቸውን ሜዳሊያዎች አድርጓል፡፡ ከመቀመጣችን በፊት፣ ሰር ሮበርት ናፒየር፣ እለት ከለት የሚለብሰውን ጠቆር ያለ ዩኒፎርም ለብሶ መጣ፡፡ እሱ እንደመጣ ትውውቅ ተደረገ፡፡ የተራራ ከባድ መሳሪያ ክፍሉ ኮሎኔል ፔን፣ የ፱ኛው ሁሳሮች ኮሎኔል ፍሬዠር፣ ካፒቴን ስፒዲ ከኒውዚላንድ የእንግሊዝ ሠራዊት አስተርጓሚና የአፄ ቴዎድሮስ ሠራዊት የቀድሞ ኮማንደር፤ ከብሪታንያ ሙዚየም አርኪዮሎጂስቶች ሚስተር ሪቻርድ ሆልምስ፣ ካፒቴን ኤስ፣ ሎርድ ሲ-ኤች፣ የካምፕ ረዳት ካፒቴን ሃርደን፣ አለም አቀፋዊው ካፒቴን ስመልፈንገስ እና እኔ ራሴ ጨምሮ፣ ከትውውቁ በኋላ ተቀመጥን፡፡ ከግዙፉ ጃይንት፣ ከካፒቴን ስፒዲ አጠገብና ከሰር ሮበርት ናፒየር ፊት ለፊት የመቀመጥ ዕድሉ አጋጠመኝ፡፡

እያንዳንዱ ሰው የራሱን መጠጫ፣ ቢላዋ፣ ሹካ፣ ማንኪያ፣ ናፕኪን ይዞ መጥቷል፡፡ ሰሀኖችና ሌሎች መገልገያዎች የጀኔራሉ ነበሩ፡፡ ዋና አሳላፊው ምክትሉና ሌላውም ሠራተኛ በደንብ የሠለጠኑ ነበሩ፤ እያንዳንዱ ሰው የሚፈልገውን ነገር ያውቃሉ፤ እናም ጠረጴዛው ዙሪያ ያለውን ጨዋታ በማያደናቅፍ መንገድ ፀጥ ባለ ሁኔታ የሚያስፈልገውን ነገር ያቀርባሉ፡፡ ሾርባው መጣ፤ የሚደነቅና ጠቀሜታ ያለው ምግብ ሆኖ የተገኘው፤ ከስንቅ ክፍሉ የአትክልት አይነቶች የተሠራ ነበር፡፡ ሾርባውን በምንመገብበት ጊዜ ለአመል ያህል እንኳን ድምፅ አልተሰማም፡፡

ባንድ ጊዜ፣ ሁላችንም መጠቻችን ወደ ጄኔራሉና ወደ እርሰ በርሳችን ካነሳን በኋላ፣ እያንዳንዳችን ያገሩን መጠጥ ቀንድ ዋንጫ ሙሉ የሚሆን ፉት ብለን በእርካታ  ጠጣን።

ሁሉም በዘመቻው የሚታወቁ ወደፊትም ሰንቀጥል የሚጠቀሱ ሰዎች ሰለሆኑ ሰለ እያንዳንዳቸው መጠነኛ ገለፃ ማድረግ ከርዕሰ የወጣ ነገር እንደማይሆን ተሰፋ እለኝ።

ጠቅላይ እዛዥ ጄኔራሉ፣ የሃምሳ ወይም የሃምሳ እምሰት ዕድሜ ሲኖረው ፊርጠም ያለና ጠንካራ ነው። ፊቱ፣ ደግነት የሚያሳዩ ሰማያዊ አይኖች ያሉበት ሲሆን፣ የሚያሳየው የደግነት ባህሪም በነዚህ አይኖች እማካኝነት ይበራል፤ በከንፈሮቹ ዙሪያ የሚታየው የማያባራ ፈገግታም ሌላ ነገር ነው። ለሁሉም ሰው፣ ሰር ሮበርት በጣም ዝም ያለ፣ ደግና ለው ወዳጅ ነው። እንዳንድ ጊዜ በድምፁ መሀል ሰርጎ የሚሰማ የእከብሮት አይነት እንደበት አለው፤ በዚህ ጊዜም ከሌላ ጊዜ ይልቅ ብዙ ቃላት ይናገራል።

ኮሎኔል ፍሬዠር፣ ትክክለኛው የወታደራዊ መኮንን ነበር፣ ራሱን ከፍ የሚያደርግ፣ ነገር ግን ምንም ጊዜ ቢሆን ትሁት ነበር፤ የማያባራ ጥንካሬ የሚያሳይ፣ ሀቀኛ፣ መልካም ባህሪና በጣም ጤነኛ ሰው ነው።

ኮሎኔል ፔን፣ በወታደራዊ ጉዳይ ልምድ ያለው ሰው ቢሆንም በዕድሜ ግን ገና ወጣት ነው። ንፁህ፣ ሰው አከባሪነትና የማይደከም ሀይል ዋና ባህሪዎቹ ናቸው።

ካፒቴን ቻርለሰ ሰፒዲ በውነቱ ግዙፍ ሰው ነው። እጆቹና እግሮቹን ሄርኩሊሰ እንኳን ቢሆን የሚቀናባቸው አይነት ናቸው። ቁመቱ ሰድሰት ጫማ ከሰድሰት ኢንች ነው። “ረዥም”፣ የሚባለው ቅፅል፣ እሱን በሚመለከት፣ የሰውየው ምኑም ላይ መለጠፍ የሚቻል ነገር ነው። ረዥም እግሮች፣ ረዥም እጆች፣ ረዥም ፂም፣ እንዲያው በሁሉም ነገር ረዥም፣ በቅርፅ፣ በሁኔታ፣ ከእርቀ ማየት መቻል በሰተቀር፤ በርግጥ በቅርብ ብቻ ማየት ሰለሚችል ሁልጊዜም ቢሆን መነፀር ማድረግ ነበረበት። ጎላ ያሉት የፊቱ ገፅታዎች፣ ከፍና ወጣ ያሉ የጉንጭ እጥንቶች፣ ዘቅዘቅ ያለ ቅንድብና፣ ቀይ የጎፈረ ፂም፣ ደግነት ያሰባቸው ሰማያዊ አይኖቹ የቆራጥነት ገፅታ ከሚያሳየው እፉ ጋር የሚነፃፀሩ ነበሩ።

ሎርድ ሲ ኤች፣ የሀያ አመት ወጣት፣ ወንዳ ወንድ ደረተ ሰፊ፣ ቁመት ያለውና ደጎሰ ያለ ሰው ነው።

ሚለተር ሆልመሰ፣ የብሪትሸ ወዶ ገብ ወይም ፈቃደኛ ሰው ነው፤ በተገኘው እጋጣሚ ሁሉ የብሪታንያን ከብር የሚያሰጠብቅ ነው። ወደ

አቢሲኒያ የመጣውም ፅሁፎችና ጥንታዊ የሆነ ስብስቦችን ለብሪታንያ ሙዝየም ለመሰብሰብ ነው::

"አሀ! ጥሩ መጠጥ ነው፣" ስፒዲ ነበር፤ በሚያሳዝን ሁኔታ እየተነፈሰ፣ ጠጁን ከፂሙ እየጠረገ ነበር፤ "በጣም ጥሩ መጠጥ ነው አላለሁ::"

"ሚስተር ስፒዲ፣ የሀገሬው ሰዎች እንዴት አድርገው ነው የሚሠሩት?" ጄኔራል ናፒየር ነበር የጠየቀው::

"መልካም፣ ጄኔራል፣ በዚህ ሀገር ጠጅ ለመሥራት በጣም የተለያዩ ዘዴዎች አሉ:: በዚህ አውራጃ፣ አንድ ኳርት የሚሆን ማር አምስት ጋሎን በሚይዝ እንስራ ውስጥ ያስቀምጡና፣ አንድ ኳርት የሚሆን ጠንካራ አረቂ ጨምረው፣ እንስራውን በውሃ ይሞሉታል፣ ከዛም ለአምስት ቀን ያስቀምጡና፣ ሁሉም ነገር ሲበስል ለመጠጥ ይደርሳል:: አፄ ቴዎድሮስ ጥሩ መጠጥ በመጥመቅ ታወቂ ነው፤ ነገር ግን በጠንካራ አረቂ ያጠነክረዋል::"

ከምግብ በኋላ የሚቀርበው ማጣጣሚያ (ደዘርት) ከዚህ የሚያስደንቅ ወግ በኋላ ቀረበ፤ ሥለ ጣፋጭ ምግቦቹ እየተወራ እያለ፣ አዛገቡ መለኛ በሆነ መንገድ ለውይይቱ የሚሆኑ ርዕሶችን ይከፍት ነበር::

ከሚስተር ሆልምስ ጋራ ስለ መንፈሳዊነት ውይይት በሰር ሮበርት በኩል ተጀመረ፤ ውይይቱ እየቀጠለ ሲሄድም ጄኔራሉ ስለዚህ ሚስጥራዊ ሳይንስ ብዙ የሚያውቅ መሆኑ ታወቀ::

ቡና ሲቀርብና፣ (የሰር ሮበርት ስጦታ) ሃባናዎች[88] ሲለኮሱ፣ ጄኔራሉ ሌላ ርዕስ ከፈተ:: ውይይቱን ሞኖፖላይዝ አድርጎ እንደያዘ መወሰድ የለበትም፤ በተቃራኒው ነው የነበረው:: ርዕሱ በአንድ ነገር ብቻ የተወሰነ አልነበርም፤ ያቀፈው፣ ሥነ ፅሁፍ፣ ስዕል፣ የሸክላ ሥራ፣ ቅርፅ፣ የቋንቋ ጥናትንም ነበር:: ከነዚህ ርዕሶች ቀስ ብለን በየደረጃው ወደ መንግሥት ጉዳዮች ተሻገርን፤ በዚህም፣ መተግበር የማይችሉ በሚደነገጉ ህጎች የሚፈፀሙ ስህተቶች በምልከአ ምድር የተያያዙ ለመሆናቸው፤ በንጉሣዊ መንግሥቶችና በሪፓብሊክ መሀከል አንፃራዊ ማበላለጥን ጨምሮ ነበር፤ ጄኔራሉም፣ ከጥንታዊ ህግጋቶችና ከዘመናዊ ድርሰቶች የተለያዩ ጥቅሶችን በማቅረብ የራሱን አመለካከት አጥብቆ ያዟል፤ በርግጥ ለእንግሊዝ ኮንስቱትሽናል ሞናርኪዝም የበላይነት በማድላት ነበር::

---

[88] ትምባሆ ጥቅል ወይም ሲጋር

## ለምዕራፍ ስድስት ተጨማሪ ማስታወሻ

*__ቁጥር 85፡__ አንጣሎ፣ የእንደርታ አውራጃ ከተማ ስትሆን፣ የአፄ ዮሐንስ (አራተኛ) ቅድመ አያት የራስ ወልደሰላሴ መዲና ነበረች። ራስ ወልደሰላሴ በሚገዙበት ጊዜ፣ ግዛቱ እስከ ቀይ ባህር ጠረፍ ድረስ ነበር። በዚያን ጊዜ ደግሞ፣ በጎንደር፣ የየጁ ተወላጅ የሆኑት፣ የትንሹ ራስ አሊ አያት ራስ ጉግሳ ነበር የሚገዙት። አንጣሎ፣ የራስ ወልደሰላሴ አባት ከራስ ስሁል ሚካኤል ሲሸሹ የተደበቁበት ሥፍራ ነበር። ራስ ወልደሰላሴ ሲሞቱ፣ ሰባጋዲስ ወንበሩን ሲይዝ፣ ሥልጣኑ ወደ አዲግራት ተዛወረ። ሆኖም ከየጁ ኦሮሞ ባላባቶች ጋር የነበረው ግብግብ ቀጥሎ፣ የራስ ጉግሳ ልጅ፣ ራስ ማርዬ፣ ከሰባጋዲስ ጋራ ባደረገው ጦርነት ማሸነፉን ሳያይ ሲሞት፣ የማርዬ ሰዎች ደግሞ ሰባጋዲስን ይገድላሉ። ራስ ማርዬን የገደለው የሰባጋዲስ ልጅ ሐጎስ ነበር። እሱም ወዲያው ተገደለ። ይህ ደግሞ ለሰሜኑ መሳፍንት፣ ለደጃች ውቤ መጠናከረ ሊጋጣሚውን ስለፈጠረ፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ትግራይን ጠቅልለው ለመግዛት አስቿሏቸዋል። ከለመንት መርካም ሲዘግብ፣ ራስ ወልደ ሰላሴን የመሰለ ጥሩ ገዥ ታይቶም አይታወቅም ይላል። በአስተዳደራቸው በጣም የሚወደዱ ነበሩ፤ የሚታመሙበት ነገር ቢኖር በስሲታምነት ነው። ነገር ግን ለድሃም ሆነ ለሌላው በሚያሳዩት የደግ አስተዳደር ስሲታምነቱ እንደ ቂም አልተያዘም። ዋና ከተማቸው ሊድዋ ቢሆንም፣ ራስ ወልደ ስላሴ ግን አንጣሎን ይወዱ ነበር። የትንሹ ራስ አሊ አጎት፣ የራስ ማርየ ጦር የነበረውን የሰባጋዲስን ሀይል ማዳከም ብቻ ሳይሆን፣ የትንሹ ራስ አሊ እናት፣ መነን፣ እንደርታና አንጣሎን ለቤልጅግ መንግሥት በ15 000 ማር ተሬዛና በ3ሺ ጠመንጃዎች ለመሸጥ ተስማምተው ነበር። (የመጨረሻው ከሰቤን ሩቢንሰን)*